የሰ/መ/ቁ. 237712

ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች፡-** ዘመን ባንክ

**ተጠሪ፡-** የከሰረው ሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማ ንብረት ጠበቂ - ጠበቃ ግርማ አለሙ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 200820 በሚያዚያ 12 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 280903 በጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የንግድ ማህበርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች በ3ኛ አመልካችነት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተጠሪ በመሆኑን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች መጋቢት 06 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ የከሰረው ሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ንብረት ጠባቂ ከዚህ በፊት ለፍ/ቤቱ ባቀረበው አቤቱታ የኪሳራ ማጣራት ስራውን አጠናቀው ለመዝጋት በየፍ/ቤቶቹ በተያዙት ክርክሮች ምክንያት የተቸገሩ በመሆኑ ክርክሮቹ በስምምነት እንዲቋረጡ ከዘመን ባንክ ጋር የተስማሙ መሆኑን በመግለጽ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ፍ/ቤቱ በ21/4/2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ የተስማሙባቸው ክርክሮች እንዲቋረጡ እና የመክሰር ሂደቱ እንዲጠናቀቅ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህም በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 161748 በአመልካች ላይ የተመሰረተው ክስ እንዲቋረጥ አቤቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱ በ24/06/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ የእርቅ ስምምነቱ በፍ/ቤቱ ማህተም ያልጸደቀ በመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም በማለት የመለሰው ስለሆነ በከሰረው ሆላንድ ካር ኃ/የተ/ግ.ማህበር የገንዘብ ጠያቂዎች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ እና በአመልካች መካከል የተደረገው ስምምነት ላይ የፍ/ቤቱ ማህተም ታትሞ በመሸኛ ጋር ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲላክ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ሚያዝያ 1 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ አስተያየት የቀረበው ውል ከከሰረው ማህበር ወኪል ጋር የተደረገ አይደለም፤ ውሉን የፈረሙት ሰዎች ውሉን እንዲያደርጉ የተሰጠ ፈቃድ ስለሌለ አቤቱታው ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካችም ይጽደቅልን ሲሉ ያቀረቡት የእርቅ ስምምነት የተደረገው በህግ እውቅና ካልተሰጠው ኮሚቴ ጋር በመሆኑ የተደረገው ስምምነት ተቀባይ የለውም ሲል የአመልካችን አቤቱታ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ የአመልካች የይግባኝ ቅሬታ ህጉ ባስቀመጠው 60 ቀናት ውስጥ የቀረበ አይደለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ህዳር 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ323(2) መሰረት የይግባኝ አቤቱታው ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቀርቧል የሚባለው የይግባኝ አቤቱታውን ለሬጅስትራሩ የቀረበበትና ተቀባይነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያገኘበት ቀን ሳይሆን ለይግባኙ ዳኘነት የተከፈለበት ቀን ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ይግባኙን መዝጋቱ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ አመልካች ቅሬታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በ8/10/2013 ዓ.ም አቅርቦ እያለ የዳኘነት የተከፈለው እና ለችሎት የቀረበው በ14/1/2014 ዓ.ም ነው በሚል የይግባኝ ጊዜ አልፎብሃል የተባለበትን አግባብ ለማጣራት የሚል ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ጥር 02 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው መልስ ይዘትም የአመልካች ይግባኝ ጊዜው ለ102 ቀናት ከ(3 ወራት) ከ12 ቀናት ያለፈ መሆኑን፤ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ቸልተኝነትና ዳተኝነት ነው ከሚባል በስተቀር የይግባኝ ጊዜው አላለፈም ሊባል የማይችል መሆኑን፤ በፍ/ሥ/ሥሕ/ቁ/325 መሰረት አመልካች የይግባኝ ጊዜው ማለፉን በተመለከተ አሳማኝ ነው የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ የሌለ መሆኑን፤ የይግባኝ አቤቱታው ተቀባይነት የሚኖረው ለፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ያቀረብኩበት ቀን (ሰኔ 8 ቀን 2013 ዓ/ም) እንጂ ዳኘነት የተከፈለበት ቀን አይደለም የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡አመልካች የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ይግባኝ አንድ የበታች ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ ሰሚ ስልጣኑ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን አለኝ የሚለውን ቅሬታ ወደሚቀጥለው በእርከን ከፍ ወዳለ ፍ/ቤት የሚያቀርብበትና ይኸው ትእዛዝ/ ፍርድ እንዲሰረዝ፣ እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የሚቀርብበት ስርዓት ሲሆን በዚህ መሰረት በይግባኝ እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ግን አቤቱታው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320(1) እንደተመለከተው የፍትሐብሔር ክርክር የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት በሌሎች ሕጎች በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የሚመራው በዚሁ ህግ በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት መሆኑን የሚያስገነዝብ እና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አስመልክቶ ዝርዝር

ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን በተመለከተም በጠቅላላው ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ60 ቀን ውስጥ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323(2) ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው የሆነው አመልካች በ60 ቀን ውስጥ ያቀረቡ መሆኑን መሰረት በማድርገ የሚከራከረው የይግባኝ አቤተታው ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘው በ60 ቀናት ውስጥ መሆኑን ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው ዳኝነት ተከፍሎ ለችሎት የቀረበው የ60 ቀን ጊዜው ካለፈ በሃለ ነው በሚል ነው፡፡ ስለሆነም ምላሽ የሚሻው ጭብጥ የይግባኝ ባይ የይግባኝ አቤቱታ ለፍርድ ቤት ቀርባል የሚባለው መቼ የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ክስ እንደቀረበ የሚቆጠረው ስለአቤቱታ አቀራረብ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሁነው ዳኝነት እንዲታይ የሚጠየቅበት የክስ ጽሁፍ ለፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት በቀረበ ጊዜ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 213/1/ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩልም ደግሞ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 467 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች በልዩ ሁኔታ በደሀ ደንብ መቅረብ እንዲችል ካልተወሰነ በቀር ዳኝነት ካልተከፈለበት በቀር አቤቱታ ተቀባይነት እንደማያገኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 215(1) ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ዳኝነት እንዲታይ የሚጠየቅበት የክስ ጽሁፍ ዳኝነት ተከፍሎበት ሲቀርብ የአቤቱታው መከፈት እና የክሱን መቅረብ የሚያመለክቱ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የይግባኝ ማመልከቻቸውን አዘጋጅተውና ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት ከፍለው ያቀረቡበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323/2/ እንደተመለከተው የ60 ቀን ጊዜ ካለፈ በሃላ መሆኑ አላከራከረም ፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ጊዜው ካለፈ በሃላ የቀረበ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ተወሰነ፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 280903 በጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**መዝገቡ ተዘግቷል**</u>፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !